# በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የኤጀንሲ ፈቃድ መስጫ፣ ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

# የሠራተኛ ምዝገባ እና ምልመላ የአሠራር ማኑዋል

ግንቦት 2009

**ሠ.ማ.ጉ.ሚ/ር**

**ማውጫ** **ገጽ**


**መግቢያ**....................2
1. **የማኑዋሉ ዝግጅትና አስፈላጊነት**....................3
2. **የተፈጻሚነት ወሰን**....................3
3. **ዓላማ** ....................4
4. **የማንዋሉ ተጠቃሚዎች** ....................4
5. **የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት**....................4
6. **የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃላፊነት** ....................5
7. **የሠራተኛ ምልመላ ምንነትና የሚያስከትለው ውጤት**....................5
8. **የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት**....................8
   8.1. **መንግስት ለመንግስት የሚደረግ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት** ....................9
   8.2. **ቀጥታ ቅጥር (በግል ጥረት የሚደረግ) የውጭ አገር ሥራ ስምሪት** ....................9
   8.3. **በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚደረግ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት** ....................10
      8.3.1. **ስለ ሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ-ሥርዓት**....................11
      8.3.2. **ጊዜያዊ የምልመላ ቦታ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ**....................12
      8.3.3. **የምልመላ አፈጻጸም ሪፖርት ስለማቅረብ**....................13
9. **የሠራተኛ ምልመላ ሂደት**....................13
10. **የቅሬታ አቀራረብ ሂደት** ....................15
11. **ከሌሎች ቡድኖች ጋር ስላለው ግንኙነት** ....................15
12. **አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ**....................16
13. **ክትትልና ግምገማ** ....................17

## መግቢያ

መንግስት መሥራት ለሚችሉ ዜጎች ሁሉ በአገር ውስጥ ሰርተው እራሳቸውን መለወጥ እንዲችሉ የሥራ ዕድሎችን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የተለያዩ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕረሮግራም፣ ፓኬጅ፣ ሕግና አሰራር በማውጣት፣ በማሻሻልና በመተግበር ጥረቶችን እያደረገ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን በመጠቀም ምርጫቸው ወደ ውጭ አገር ሄደው ለመሥራት ለሆነ ዜገች መሥራት እንዲችሉ የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ አውጥቶ ወደ ተግባር መግባቱ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኤጀንሲ ፈቃድ መስጫ፣ ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ በተለይም የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ህግና ስርዓትን ተከትሎ ዜጎች ከብዝበዛ፣ አድሎ እና ወጥነት ከሌለው አሰራር የጸዳ የምልመላ ሥነ-ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ የአሰራር ማኑዋል አዘጋጅቷል፡፡

ይህ የምዝገባና ምልመላ የአሠራር ማኑዋል ዜጎች ከአገልግሎቱ ተገቢውን ቀልጣፋና ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያመቻች፣ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን የሚከላከል እና በየደረጃው ለሚፈጠሩ የአሰራር ችግሮች የተጠያቂነትና የኃላፊነትን ሁኔታ ለማመላከትና በአዋጁና በአፈጻጸም መመሪያው ብሎም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች ላይ የተመለከቱ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ/የሚያግዝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ዜጎች ከምልመላና ምዝገባ ጋር በተያያዘ ሂደት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መረጃ ለመስጠትና በሂደቱ ውስጥ

ለሚደርስባቸው ያልተገባ የምልመለና ምዝገባ ችግር ወይም ቅሬታ እንዴት ማቅረብና የአፈታቱን ሂደት በማሳየት መብታቸውን ለማስጠበቅ እንዲረዳ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

## 1. የማኑዋሉ ዝግጅትና አስፈላጊነት

ይህ ማኑዋል የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅን፣ የአዋጁን የአፈጻጸም መመሪያ፣ አግባብነት ያላቸውን ህጎችን እንዲሁም የሌሎች አገራትን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱን ዓላማ፣ ራዕይና ተልኮ ለማሳካት የሚጠበቁ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን በግልጽነትና በታማኝነት ለማስፈጸምና ለመምራት ሥርዓት ለማስያዝና የአፈፃፀም ጊዜ ገደብ መወሰን ተገቢ በመሆኑ፣

በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች አማካኝነት ዜጎች ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት ምዘገባና ምልመላ ሲያከናውኑ በህግና በስርዓት መምራት አግባብ ሆኖ በመገኘቱ፣

አገልግሎት ፈላጊው ተገልጋይ እና አገልግሎት ሰጪው በመስሪያ ቤቱ ላይ እምነትና ከበሬታ እንዲኖረው የተቋሙ ፈጻሚ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች አገልግሎት በሚሰጡበት ሂደት ውስጥ ግልጽ ቀልጣፋና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ የሚመሩበት የአሰራር ማኑዋል በማስፈለጉ፣

## 2. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የአሰራር ማኑዋል በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች፣ በክልል ሰ.ማ.ጉ መ/ቤቶች  በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች፣ አሠሪዎች እንዲሁም የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት ፈላጊዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## 3. ዓላማ

የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት የሚመለምሏቸውን ሠራተኞች ወጥነት ባለውና ህግና ስርዓትን በጠበቀ መልኩ የምዝገባና ምለመላ ሂደት የማከናወን ሥነ-ስርዓት እንዲኖር፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ግልጽ አሰራር በማስፈን የተገልጋዮችን እርካታ በማሳደግ ህገ ወጥ የሠዎች ዝውውርን መከላከል ነው፡፡

## 4. የማንዋሉ ተጠቃሚዎች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የክልል ሠ.ማ.ጉ. መ/ቤቶች፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች፣ ሥራ ፈላጊዎች እና ሌሎች የዚህ የምዝገባና ምልመላ ሥነ-ስርዓት የአሠራር ማንዋል ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

## 5. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት

- ከሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ጋር በተያያዘ ለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- ኤጀንሲዎች የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ስነ ሥርዓት እንዲያዘጋጁና እንዲያጸድቁ ማገዝና መደገፍ፣,
- ኤጀንሲዎች ያዘጋጁትን የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ ሥርዓት መርምሮ ማጽደቅ፣
- ኤጀንሲዎች ባጸደቁት የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ ሥርዓት መሰረት ሥራቸውን እያከናወኑ መሆናቸውን መከታተል፣ መቆጣጠርና ማረጋገጥ፣

- የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሂደት ቀልጣፋና ፍትሃዊ ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከሌሎች አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ ተቋሙ ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ያለውን የትብብርና የቅንጅት አሰራር ማጠናከር፣
- ከሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዲሁም የተሰጡ መፍትሄዎችን በየጊዜው በመመዝገብና በማደራጀት በመረጃነት መያዝ፣
- የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሂደት ከመስሪያቤቱ ስትራጂክ ዕቅድ ጋር በማቀናጀት አገልግሎቱን በየጊዜው የማሻሻል እርምጃ መውሰድ፣

## 6. የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃላፊነት

- የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን የተመለከቱ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ሥርዓቶችን የማወቅና ተግባራዊ የማድረግ፣
- ማንኛውም ኤጀንሲ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሥራ ፈላጊዎችን የምዝገባና የአመላመል ሥነ ስርዓት አዘጋጅቶ ማጸደቅ እና ተገቢውን የምዝገባና ምልመላ ባለሙያ መመደብ፣
- ከመስሪያቤቱ የበላይ ኃላፊዎች፣ ቡድን መሪዎችና ሠራተኞች የሚተላለፉ መመሪያዎች፣ አሰራሮችና ትዕዛዞችን የማክበርና የመፈጸም፣

## 7. የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ምንነትና የሚያስከትለው ውጤት

የሠራተኛ ምልመላ የሚከናወነው በሁለት መንገድ ሲሆን አንደኛው በሕጋዊ መንገድ የሚደረግ የሠራተኛ ምልመላ ሲሆን ሌላኛው በሕገ ወጥ መንገድ የሚደረግ የሠራተኛ ምልመላ በመባል ይታወቃል፡፡ ሕጋዊ የሠራተኛ ምልመላ ህግና ስስዓትን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ፈቃድ ኖሮት ሥራውን እንዲያከናውን በከፈተው

ቢሮ ብቻ ላገኘው የሥራ ዕድል ብቁ የሆኑ ዜጎችን ፍትሃዊነትና ግልጽነት ባለው ሁኔታ ክፍት የሥራ ቦታው የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች እንዲሁም ጥቅማ ጥቅሞች ከማስታወቅ አንስቶ ሥራ ፈላጊዎችን መመዝገብ፣ መምረጥ፣ መመልመልና ለሥራ ማሰማራት ሲሆን፡፡

የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ዋና ዓላማም ለተፈለገው ክፍት የሥራ ቦታ በተትምህርት፣ በዕውቀት፣ በችሎታና በክህሎት ለሥራው የሚመጥን ብቁ ተወዳዳሪን በመምረጥ ለሥራው ተስማሚ የሆነ ሠራተኛን መርጦ በህጉ መሰረት ለሥራ ማሰማራት ነው፡፡

ሌላኘው ሕገ-ወጥ የሠራተኛ ምልመላ ሲሆን “ሕገ-ወጥ የሠራተኛ ምልመላ›› ማለት ህጋዊ የኤጀንሲ ፈቃድ ሳይኖር ሕግና ስርዓትን መሰረት ባላደረገ ሁኔታ ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት ሠራተኛን በየቦታው መመልመል፣ መመዝገብ፣ ማቆየት፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ መቅጠር ወይም ማስቀጠር፣ የአገልግሎት ኮንትራት መስጠት፣ ተስፋ መስጠት ወይም ማስታወቂያ ማውጣት ነው፡፡ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለ|መከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ 909/2007 ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ከዚህ እንደሚከተለው ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውጪ ለብዝበ ዓላማ ሲባል፡-

1) በአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት ወይም ለሥራ ወይም ለሥራ ልምምድ ወደ ውጭ አገር መላክ በሚል ሽፋን፣
2) የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ ወይም በጉዲፈቻ ሽፋን፣ ወይም
3) ለሌላ ማንኛውም ዓላማ

ዛቻን፣ ኃይልን ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በማገት፣ በመጥለፍ፣ በተንኮል፣ በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ሥልጣንን አላግባ በመጠቀም፣ የሰዎችን ለጥቃት ተገላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማገኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል ሰዎችን መመለመል፣ ማዳዳዝ፣ ማዘዋወር፣ ማስጠለል ወይም መቀበል ነው፡፡

ይህ በአንዲህ እንዳለ የኤጀንሲ ፈቃድ ኖሮት ፈቃድ ወዳልተሰጠው አገር፣ ያገኘውን የሥራ ዕድል ሳያጸድቅ፣ የኤጀንሲነት ፈቃዱን ሳያሳድስ፣ ከከፈተው ቢሮ ውጪ እና ቅርንጫፍ ቢሮ ባልከፈተበት ክልል ሠራተኛን መመልመል፣ ሠራተኛው ለሥራ በሚሰማራበት የሥራ መስክ ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ የሌለውን ሠራተኛ መመልመል፣ የትምህርት ደረጃው ቢያንስ ስምንተኛ ክፍልን ያላጠናቀቀ ሠራተኛ መመልመል፣ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነን ሠራተኛን መመልመልና በኢትዮጵያ እና በተቀባይ አገር መካከል የሠራተኛ ቅጥር የሁለትዮሽ ስምምነት ከተፈፀመበት አገር ውጭ ወይም ሚኒስቴሩ ሠራተኛ ለሥራ እንዳይሰማራ ወደ ከለከለበት አገር ሠራተኛን ለመላክ መመልመል ወይም ማሰማራት፤ የሕዝብን ጤና ወይም ሞራል በሚጎዳ ወይም የአገሪቷን ክብርና ገፅታ ለሚያጎ ድፍ ሥራ ሠራተኛን መመልመል ወይም ማሰማራትና የመሳሰሉትን ድርጊት ማከናወንም ሕገ-ወጥ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ድርጊት ነው ይህንንና ከላይ የተጠቀሱትን መፈጸም በተመለከተ ሕገ-ወጥ የሰዎቸ ዝውውር እና ሰደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ደንበር ማሻገር ወጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጣር በወጣው አዋጅ ቁጥር 909/2007 ላይ ወንጀል መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ይህን ወንጀል ፈጽሞ በተገኘ ሰው ላይም ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 150,000 እስከ 300,000 በሚደርስ መቀጮ እንደሚቀጣ በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን ወንጀሉ የተፈጸመው በሕጻናት፣ በሴቶች ወይም በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ እና በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል ለ - ሠ ከሆነ ከብር 200,000 እስከ 500,000 በሚደርስ መቀጮ እና ከ25 ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት ወይም ዕድሜ ልክ እስራት እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

## 8. የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት

የውጭ አገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት በኢትዮጵያ ከ1990 ዓ.ም በፊት ይሰጥ የነበረው ግለሰቦች፣ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ውል እንዲጸድቅላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለና አገልግሎቱን ፈላጊዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ አገልግሎቱ በሕግና በአሰራር መመራት እንዳለበት በመታመኑ ለመጀመሪያ ጊዜ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 104/90 እንዲወጣ ተድርጎ ለአስር ዓመታት ያህል ሲሰራበት ቆይቶ በአፈጻጸም ሂደት ውስጥ በታዩበት አንዳንድ ችግሮች ምክንያት በሌላ አዋጅ መተካት በማስፈለጉ የሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 632/2001 ወጥቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሲሰራበት እንደነበር የሚታወቀ ነው። ይሁንና ይህ አዋጅ በሚተገበርበት ወቅት ከጊዜ ወደ ጊዜ በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው አደጋ (የመብት ጥሰት፣ ብዝበዛ፣ ሞት፣ የአካል ጉዳትና የአካል መጓደል፣ እንግልት፣ ወ.ዘ.ተ) ተባብሶ የታየ ሲሆን ለዚህም በዋናነት ተጠቃሽ የነበሩት ምክንያቶች በዘርፉ የተሰማሩት ኤጄንሲዎች በተለያዩ ምክንያቶች የዜጎችን መብት፣ ክብርና ደህንነት በሚፈለገው መልኩ ማስጠበቅ አለመቻል፣ የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን በብቃትና በተገቢው ለመምራትና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ የሕግ ማዕቀፍና ተቋማዊ አደረጃጀት ባለመኖሩ ነበሩ።

በአጠቃላይ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ባሉበት ክፍተቶችና የአፈፃጸም ችግሮች ምክንያት በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ ዜጎች መብት፣ ደህንነት፣ ክብርና ጥቅም በሚፈለገው ደረጃ ለማስጠበቅ አላስቻለም፣ በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ዙሪያ የሚታዩ የሕግ፣ የአሰራርና የአደረጃጀት ችግሮች እስኪፈቱ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆም በመንግስት ተወስኖ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን በዚህ ጊዜም የነበሩትን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት፣ የሌሎች አገራትን ተሞክሮ በመቀመር በቅርቡ የአትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 ሊወጣ ችሏል። አዲስ በወጣው የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት

አዋጅ እንደተመለከተው ሶስት ዓይነት የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት እንደሚሰጥ ያመለክታል እነዚህም፡-

1/ መንግስት ለመንግስት የሚደረግ

2/ ቀጥታ ቅጥር (በግል ጥረት የሚደረግ) እና

3/ በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚደረግ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ናቸው፡፡

## 8.1. መንግስት ለመንግስት የሚደረግ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት

የሥራ ስምሪት አገልግሎት በመንግስት በኩልም በስፋት የሚሰጥ ሲሆን በዚህ አገልግሎት አማካኝነት አገልግሎት የሚሠጠው ተቀባይ አገር ብዛት ያለው የሠራተኛ ኃይል ይቅረብልኝ ጥያቄ ለሚኒስቴሩ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመተባበር መንግስት - ለመንግስት የሚደረግ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ መንግሥት ለመንግሥት በሚደረግ ስምምነት መሠረት በተቀባይ አገር ለሚገኝ መንግሥታዊ ድርጅት የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎቶችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሚኒስቴሩ አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመተባበር የሚሰጠው የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎቶች ማስታወቂያ ማውጣትን፣ ምዝገባና ምልመላ ማካሄድን፣ ቃለ መጠይቅና መረጣ ማድረግን፣ የጤና ምርመራ እንዲከናወን ማድረግን፣ የሥራ ውል ማፅደቅን፣ የቅድመ-ቅጥር እና ቅድመ-ጉዞ ገለፃ መስጠትን፣ የተቀጣሪ ሠራተኛ የውጭ ጉዞ ማመቻቸትን እና የመሳሰሉትን ሌሎች አገልግሎቶችን ይጨምራል፡፡

## 8.2. ቀጥታ ቅጥር (በግል ጥረት የሚደረግ) የውጭ አገር ሥራ ስምሪት

በግል ጥረት ወይም ቀጥታ ቅጥር የውጭ አገር ሥራ ስምሪት የመንግሥታዊ አካል ወይም የኤጀንሲ አገልግሎት ሳይሰጥ አሠሪውና ሠራተኛ በራሳቸው በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈፀም ቅጥር ነው ማንኛውም አሠሪ በሚኒስቴሩ ወይም በኤጀንሲ በኩል ካልሆነ በቀር ሠራተኛን በቀጥታ መልምሎ መቅጠር የተከለከለ ቢሆንም አሰሪው የኢትዮጵያ ሚሲዮን አባል፣ ዓለም አቀፍ ድርጅት ከሆነ እንዲሁም ከየቤት ሠራተኛነት በስተቀር ማንኛውም ሥራ ፈላጊ በራሱ ጥረት ሥራ ፈልጎ ሲያገኝ ቀጥታ ቅጥር ይፈቀዳል። ከየቤት ሠራተኛነት በስተቀር ማንኛውም ሥራ ፈላጊ በራሱ ጥረት የሥራ ዕድል ሲያገኝ ሊፈቀድለት የሚችለው ከዚህ የሚከተሉት ሲሟሉብቻ ነው፡-

1. ሠራተኛው በሚሄድበት አገር መብቱ፣ ደህንነቱና ክብሩ ሊጠበቅ እንደሚችል በሚመለከተው ሚሲዮን ወይም በተቀባዩ አገር ሚሲዮን ከሌለ አዲስ አበባ በሚገኘው የተቀባዩ አገር ሚሲዮን እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ፣
2. በአዋጁ መሠረት የተገባ የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሣ ኢንሹራንስ ሽፋን ስለመኖሩ፣ እና
3. ከሥራ ውሉ ጋር ምቹ የሆነ የአየር ወይም የየብስ መጓጓዣ አገልግሎት የሚያገኝ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው።

በአዋጁ መሠረትም ቀጥታ ቅጥር እንዲፈፅም ለተፈቀደ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ሊወጣ የሚችለው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን በኩል ብቻ ሲሆን ዜጎች ከላይ የተጠቀሱትን መሽፈርቶች በሟሟላት ለሚኒስቴሩ የሥራ ውላቸው እንዲጸድቅላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ሚኒስቴሩም ጥያቄያቸውን መርምሮ በማጽደቅ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል።

## 8.3. በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚደረግ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት

መንግስት ለመንግስት ከሚሰጠው የሥራ ስምሪት አገልግሎት በተጨማሪ የግሉ ሴክተር በዘርፉ የላቀ ሚና እንዳላቸው ቀደም ሲል ከነበረው የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ መረዳት ይቻላል

በመሆኑም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በዚህ ዘርፍ ሊኖራቸው ስለሚገባ ሚና በህግ በተወሰነው መሠረት ማንኛውም ኤጀንሲ በህጉ መሰረት ፈቃድ አውጥቶ ዜጎችን ይህን አገልግሎት መስጠት እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ማንኛውም ብቁ የሆነ ሰው ፈቃድ በማውጣት አገልገሎቱን መስጠት የሚችል ሲሆን ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት ዜጎችን ከመመልመሉ በፊት ማንኛውም ኤጀንሲ በአዋጁ መሰረት የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ ስርዓት አዘጋጅቶ ማጸደቅ ይኖርበታል፡፡

ይህ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ ስርዓት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ ከዚህ በታች የሚከተሉትን በዋነኝነት የያዘ መሆን ይኖርበታል::

### 8.3.1. ስለ ሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ-ሥርዓት

**1. ማንኛውም ኤጀንሲ የሚያቀርበው የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ ስርዓት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትን በዋነኝነት መያዝ ይኖርበታል፡-**

ሀ. የሥራ ማስታወቂያ አወጣጥ ሁኔታ፣

ለ. የሠራተኛው የዕድሜ ሁኔታ፣

ሐ. የአመልካቾች አመዘጋገብ ምልመላና መረጣ ሂደት፣

መ. የግልጸኝነትና የተጠያቂነት አሰራር የሚከተል መሆኑን፣

ሠ. የሠራተኛ ምልመላ በአገሪቱ የሰው ኃይል ፍላጎት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማያስከትል መሆኑን፣

ረ. ለተመልማዩ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሠራተኛው ከሚቀጠርበት ሥራ ጋር ብቻ ግንኙነት ወይም ተዛማጅነት ያላቸው መሆኑን፣

ሰ. በሠራተኛ ምልመላና መረጣ ወቅት በጾታ፣ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በቀለም፣ በጎሳና በመሳሰሉት ምንም ዓይነት አድሎ የማይደረግ መሆኑን፣

ሸ. ማንኛውም ኤጀንሲ በምዝገባና በምልመላ ጊዜ ያገኘውን የሠራተኛ መረጃ በሚስጢር የሚይዝ መሆኑን ይኖርበታል፡፡

**2.** ማንኛውም ኤጀንሲ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ማካሄድ የሚችለው በተፈቀደለት ክልል በከፈተው ቢሮ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

### 8.3.2. ጊዜያዊ የምልመላ ቦታ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ

1) ማንኛውም ኤጀንሲ የሚፈጽመው የሠራተኛ ምልመላ ብዙ የሰው ኃይል የሚጠይቅ ከሆነ ጊዜያዊ ምልመላ የሚያካሂድበትን ቦታ፣ ምለመላው የሚወስደው ጊዜ፣ የሚመለመሉ ሠራተኞች ብዛት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች አስመልክቶ ጥያቄውን በጽሁፍ እንዳግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሰልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

የሚቀርበው ጊዜያዊ የሠራተኛ ምልመላ ቦታ ፈቃድ ጥያቄ ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተሉትን በዋነኝነት መያዝ ይኖርበታል፡፡

ሀ. የተገኙ ክፍት የሥራ መደቦች ዓይነትና ብዛት፣

ለ. የተገኙ ክፍት የሥራ መደቦች የሚጠይቁት ተፈላጊ ችሎታ፣

ሐ. የሚመለመሉ ሠራተኞች ብዛት፣

መ. ምልመላው የሚካሄድበት ቦታ፣

ሠ. ምልመላው የሚወስደው ጊዜ፣

2) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሰልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቀረበለትን ጥያቄ በመመርመር ጥያቄው በቀረበለት በ2 (ሁለት) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

### 8.3.3. የምልመላ አፈጻጸም ሪፖርት ስለማቅረብ

ማንኛውም ኤጀንሲ በከፈተው ቢሮ ወይም በተፈቀደለት ጊዜያዊ የምልመላ ቦታ ያካሄደውን የምልመላ አፈጻጸም ሪፖርት ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው ፎርማት መሰረት ምልመላው በተጠናቀቀ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ እንደ አግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

## 9. የሠራተኛ ምዝገባ፣ ምልመላና ስምሪት ሂደት

የሠራተኛ መዝገበና ምልመላ ሂደት ሊከናወን የሚችለው በቅድሚያ ማንኛውም ኤጀንሲ ከተቀባይ አገር ያገኘውን የሥራ ዕድል /Job Order/ በቅድሚያ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው ባለስልጣን አቅርቦ ማጸደቅ ይኖርበታል፡፡ በመቀጠልም ህጉ ላይ በተመለከተው መሰረት ለክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ በማናቸውም የመገናኛ ብዙኃን ሲወጣ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ) የኤጀንሲውን ስም፣ አድራሻ፣ በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ ቁጥር እና ሠራተኛ ለመላክ የተፈቀደለትን አገር፤

ለ) ስለተገኘው ክፍት የሥራ መደብና ብዛት፣ተፈላጊ ችሎታ፣ የደመወዝ መጠን፣ የቅጥር ቆይታ ጊዜ፣ሥራው የተገኘበት፣ አገር፣ ቦታ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፤

ሐ) ኤጀንሲው ለሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሠራተኛውን ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ የማያስከፍል ስለመሆኑ መግለጫ፡፡

በዚሁ መሰረት ሥራ ፈላጊዎችን መመዝገብ እና በመስፈርቱ መሰረት ብቁ ተወዳዳሪዎችን በግልጽነትና በፍህታዊነት አወዳድሮ በመምረጥ በህጉ መሰረት ለሥራ ማሰማራት ነው፡፡

ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ማንኛውም ሠራተኛ ቢያንስ ስምንተኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ እና በሚቀጠርበት የሥራ መስክ አግባብነት ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ይህንን ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚጠየቀው አሠሪው የሚጠይቃቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሠራተኛ የጤና ምርመራ የሚደረገው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚመርጠው የጤና ተቋም ብቻ ሲሆን፡፡

1. ኤጀንሲው ሠራተኛን ለጤና ምርመራ መላክ ያለበት አሠሪው የሚጠይቃቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡
2. ሠራተኛው ከአንድ ጊዜ በላይ የጤና ምርመራ እንዲያደርግ የሚጠየቅ ከሆነ ወጪውን ኤጀንሲው መሸፈን ይኖርበታል፡፡

ማንኛውም ኤጀንሲ ዜጎችን መመልመል የሚችለው በከፈተው ቢሮ ብቻ እንደሆነ ቀደም ሲል የተጠቀሰ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ኤጀንሲው ዜጎችን በሚመለምልበት ክልል ቅርንጫፍ ቢሮ መክፈት ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት ዜጎችን በመለመለበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ለክልሉ/ለከተማ አስተዳደሩ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤት የመለመላቸውን ዜጎች ዝዝር መግለጫ ማቅረብና የክልሉን/የከተማ አስተዳደሩን ይሁንታ በማግኘት ለቀጣይ የውል ማጽደቅ ሂደት ህግና ስርዓቱን በጠበቀ ሁኔታ ለሚንስቴር መ/ቤቱ አቅርቦ በማጸደቅ ሠራተኛውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሥራ ማሰማራት ይኖርበታል፡፡

ወደ ውጭ አገር ለሥራ የላከውን ሠራተኛ በሚሄድበት አገር ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት በ15 (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ አሳውቆ የማስመዝገብ፣ የሥራ ፈቃድና የመኖሪያ ፈቃድ ስለማግኘቱ የማረጋገጥና ይህንኑ መረጃ አሟልቶ ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ በአንድ ወር ጊዜ

ውስጥ ኤጀንሲው ሠራተኛን ወደ ሥራ ማሰማራት ካልቻለ የጸደቀው የሥራ ውል እንዲሰረዝ ከነምክንያቱ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 10.የቅሬታ አቀራረብ ሂደት

ማንኛውም ከሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ጋር በተያያዘ የተጎዳ ሠራተኛ ወይም የተጎጂው ሠራተኛ ተወካይ ከሠራተኛ ምልመላና ምዝገባ ጋር በተያያዘ አዋጁን እና በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ሌላ ተዛማጅነት ያለው ሕግ በኤጀንሲው፣ በባለሙያው፣ በኃላፊው ወይም በአመራሩ ተጥሷል በሚል ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን አቤቱታውን በጽሁፍ ወይም በቃል ማቅረብ የሚችል ሲሆን የቅሬታው አቀራረብና አፈታት ሥርዓቱም በሚከተለው አግባብ ይፈጸማል፡፡

10.1. ቅሬታውን በመጀመሪያ አገልግሎት ለሰጠው ባለሙያ ያቀርባል፤ ባለሙያው በሰጠው ምላሽ ካልረካ

10.2. ቅሬታውን በቀጥታ አገልግሎት ለሰጠው ባለሙያ ቡድን አስተባባሪ ያቀርባል፣

10.3. ቅሬታ አቅራቢው ከቡድን መሪው በተሰጠው ምላሽ ካልረካ አገልግሎት ለሰጠው የሥራ ሂደት ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

10.4. ቅሬታ አቅራቢው ከሥራ ሂደቱ ዳይሬክቶሬቱ በተሰጠው ምላሽ ካልረካ ለመ/ቤቱ የሥነምግባር መኮንን መግለጽ/ማቅረብ ይችላል፣

10.5. ከላይ በተሰጠው ምላሽ ካልረካ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በየደረጃው ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፣

10.6. ቅሬታ አቅራቢው በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመጨረሻ በተሰጠው ምላሽ/ውሳኔ ካልረካ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት፣ ለህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም፣ ለሰብአዊ መብት፣ ለሚዲያ አንዲሁም ለሌሎች ለሚመለከታቸው ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፣

## 11.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስላለው ቅንጅታዊ አሰራር

የሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ ለሥራ የሚያደርጉት ዝውውር /Labour Mobility/ ዘርፈ ብዙና ውስብስ ሂደት መሆኑ ይታወቃል ስለሆነም ይህን ውስብስብና ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እንዲሁም ህግና መሰረትን የተከተለ ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መተባበርና መቀናጀት ወሳኝነት ስላለው በተቋሙ ውስጥም ይሁን ከተቋሙ ውጪ ካሉና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ውጤታማ ቀልጣፋ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት እንዲኖር የማድረጉ ሥራ እንዳለ ሆኖ በተለይም ህጋዊ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሂደትን ለማሳለጥ ቡድኑ ከሌሎች ቡድኖች ጋር በተለይም ከቁጥጥር ክትትልና ድጋፍ፣ ከአቤቱታ ክትትልና ድጋፍ፣ ከውል ማጽደቅ እንዲሁም ከትምህርትና ሥልጠና ቡድኖች ጋር እንዲሁም ከፍትህ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት በመሥራት ዜጎች ለብዝበዛ፣ ለአድሎ፣ ለእንግልት ብሎም ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዳይዳረጉ የትብብር የቅንጅት አሰራርን በማጠናከር ይሰራል፡፡

## 12.አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕገ-ወጥ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላን ለመከላከል ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማንኛውም ዓይነት ሕገ-ወጥ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ድርጊት ስለመከናወኑ በአካል ወይም በስልክ ጥቆማ፣ አስተያየትና ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመቀበል እና በተለያየ ሁኔታ ድርጊቱ መፈጸሙ ሲታወቅ መረጃና ማስረጃዎችን በማደራጀት እና ሚስጥራዊነቱን በመጠበቅ ወዲያውኑ እንደአግባቡ ለኤጀንሲ ፈቃድ መስጫ፣ ቁጥጥር ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት፣ ለሕግ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ለበላይ ኃላፊዎች በማሳወቅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንደ ድርጊቱ ሁኔታ ህግና ስርዓትን መሰረት በማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድና ከዚያም በላይ አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ እንዲጠየቅ የማድረግ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 13.ክትትልና ግምገማ

አንድ ኤጀንሲ ፈቃድ አውጥቶ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ አሰራር ስርዓት በማዘጋጀት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርቦ የሚያጸድቅበት ሁኔታ በአዋጁ እንዳለ የሚታወቅ ሲሆን ይህን የአሰራር ስርዓትም በመከተል መስራቱን ሕገ-ወጥ የሠራተኛ ምልመላ መከላከያ ቡድን ከመነሻው ጀምሮ የማጸደቁን፣ የመከታተሉንና የመገምገን ሥራ አጠናክሮ የሚሰራው ሲሆን በተለይም የኤጀንሲ ቁጥጥር ቡድን ከሚያደርጋቸው ቁጥጥሮች ጋር በማቀናጀት የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ህግና ስርዓትን ተከትሎ መሰራቱን የማረጋገጡ ሥራ በቡድኑ የሚሰራ ሲሆን ህግን ላከበሩ የማበረታታት ከህግና ከስርዓት ውጭ የሆኑትን የመደገፍ የማብቃት ከዚያም በላይ ሲሆን እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ህግን መሰረት በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ብሎም የህግ ውሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡